MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም ሂደት (IEP) ላይ ያለዎትን ተሳትፎ ያጠናክሩ።

## 1 የወላጅ ሪፖርት

ከ K–12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች፣ የ MCPS ቅጽ 336-39 ይሙሉ፣ የወላጅ ሪፖርትለቡድኑ ተጨማሪ ሃሳቦችን እንዲሰጡ ጥሪ ከተደረገልዎት ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ ተልኳል። ቅጽ 336-39 በ MCPS ድረ-ገጽwww.montgomeryschoolsmd.org Parent Report 336-39 ላይ ይፈልጉ/ያገኙታል። ለቅድመ ምዋእለ ህፃናት ተማሪዎች፣ የሚሞሉት የጥንካሬ እና የፍላጎት ማጠቃለያጥሪ ከተደረገልዎት ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጓል። የተሞሉትን ቅጾች ከስብሰባው በፊት ጉዳዩን ለሚከታተለው/ለምትከታተለው (ኬዝ ማናጀር ) በኢ-ሜይል ወይም ልጅዎ ለሚማርበት ት/ቤት መልሰው ይላኩ።

## 2 ረቂቅ ሰነዶች

የ IEP ረቂቅ ሰነዶች ከIEP ስብሰባ አምስት ቀናት በፊት ይደርስዎታል። ከስብሰባው ቀን በፊት ሰነዶቹን ያንብቡና በስብሰባው ወቅት ለማንሳት የሚፈልጓቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎች ወይም ያለዎትን ስጋት ይፃፉ። እነዚህን ሰነዶችን ለማግኘት የማይፈልጉ ከሆነ በቅድሚያ ለማሳወቅ ይችላሉ።

## 3 ወቅታዊ የአካዳሚያዊ/የትምህርት ስኬታማነት እና የተግባር አፈፃፀም ደረጃዎች (Present Levels of Academic Achievement and Functional Performance) (PLAAFP)

ልጅዎ ስላለው/ስላላት ጥንካሬ እና ፍላጎት የሚያረጋግጡ በርካታ የመረጃ ምንጮች በ (PLAAFP) ውስጥ መካተት አለባቸው። ተጨማሪ የትምህርት እና የባህርይ/ስነምግባር መረጃ በ (PLAAFP) ላይ እንደአስፈላጊነቱ እንዲጨመር ለመጠየቅ ይችላሉ።

## 4 የማስተማሪያ እና የምዘና መዳረሻ ባህሪያት እና ስፍራ/ማመቻቸቶች፣ ተጨማሪ ድጋፎች፣ አገልግሎቶች፣ የፕሮግራም ማሻሻያዎች እና እርዳታዎች/ድጋፎች

ስለ IEP ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮችን በደንብ ለማወቅ/ለመረዳት የ IEP ቡድኑን ይጠይቁ። እነዚህም የሚያካትቱት፡

- የመዳረሻ ገፅታዎች
- ዝግጅቶች
- ተጨማሪ እርዳታዎች እና አገልግሎቶች
- የፕሮግራም ማሻሻያዎችና ድጋፎች

እነዚህ ነገሮች (features/accommodations/aids and services/modifications) ምን ምን እንደሆኑ እና ልጅዎ እንዲጠቀምበት/እንድትጠቀምበት አስፈላጊ(አግባብ) የሆነበትን ምክንያት እንዲገለጽልዎት ቡድኑን ይጠይቁ።

## 5 ዓላማዎች:-

የዓላማ እና ግብ ክፍልን ሲያነቡት፣ ያለዎትን ማንኛውንም ጥያቄ ይጻፉ። በስብሰባው ወቅት እነዚህን እና ሌሎችንም የሚያስቧቸውን ጥያቄዎች ለማንሳት/ለመጠየቅ እርግጠኛ ይሁኑ።



0579.18 • Amharic